



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
# 6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ውጤት

ሐምሌ 03 ቀን 2013
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ

www.nebe.org.et



**መግቢያ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በድጋሚ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ተቋማዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ኦፐሬሽን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ለውጦችን እንዳከናወነ ይታወቃል። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ይህንን አገራዊ ምርጫ ያከናውነውን ስራ አመራር ቦርድ አባላት ስራ መጀመር፣ የምርጫ፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና ስነምግባር አዋጅ 1162/2011 በሰፊ ምክክር መፅደቅ፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች ድጋሚ ምዝገባ መጠናቀቅ እንዲሁም ከ30 በላይ የሆኑ ምርጫን የሚመሩ መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና ስራ ላይ ማዋል ከመሰረታዊ የምርጫ ስራዎች ዋና ዋና ነበሩ። ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለ6ተኛው ምርጫ ከመዘጋጀት የተረከበውን በዝቅተኛ አቅም ላይ የሚገኝ ተቋም ምርጫን በገለለግተኝነት ለመምራት የሚችል ተቋም ማድረግ ከሰው ሃይልን ከማደራጀት እና ሃብትን ከመሰብሰብ አንጻርም ቁጥራቸው ከፍተኛ አጋር ድርጅቶችን ለማፍራት አያሌ ጥረቶችን አድርጓል።

በዚህ ሂደት ውስጥ የህጎችን መሻሻል ስራውን በማገዝ፣ ምርጫውን ለማዘመን እና በገለልተኝነት ለመምራት የሚያስችለውን በጀት በመፍቀድ ረገድ የኢ.ፌ.ዴ. ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና መንግስትም ከፍተኛውን አስተዋእጽኦ አድርገዋል።

**የምርጫ እቅድ እና ዝግጅት**

እንደሚታወቀው 6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ከመነሻው አንስቶ በመደበኛ ጊዜ እና ሁኔታ ከተካሄዱት ምርጫዎች መካከል የተለየ እንደሚሆን ግልጽ ነበር፣ ምርጫው እጅግ በጣም ብዙ ፓለቲካዊ እና ማህበረሰባዊ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሊከናወን እንደነበር ቦርዱ አውቆ ዝግጅቱን የጀመረ ቢሆንም የአለም አቀፍ ኮቪድ ወረርሽኝ ስጋት ከታሰበበት ጊዜ በ10 ወር ዘግይቶ እንዲካሄድ ማድረጉ ደግሞ በተጨማሪነት የምርጫውን ሂደት እቅድና ዝግጅት እንዲሁም ጊዜ እንደአገርም እንደቦርድም ካሰብነው የተለየ እንዲሆን አድርጎታል።

ቦርዱ 6ተኛው አገራዊ ምርጫ በጥር ወር 2012 ዓ.ም ጊዜ ሰሌዳን አውጥቶ እና ምርጫው በነሃሴ 23 ቀን 2012 እንደሚከናወን ይፋ አድርጎ የተወሰኑ ተግባራትን ካከናወነ በኋላ በአለም አቀፉ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በአገራችን መከሰት የተነሳ ሊከናወን የነበውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ወደፊት እንዲገፋ ሆኗል። በዚህም ወቅት ለኮቪድ ወረርሽኝ ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ሃብቶችን ከማስፈለጉ ጀምሮ እጅግ የተለወጡ ማህበራዊ እና ፓለቲካዊ ሁኔታዎች በዚህ አመት ያከናውነው ምርጫ ስኬት ላይ ተጽእኖ እንዳያደርጉ ቦርዱ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

በመስከረም ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ. ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ በ2013 ዓ.ም እንዲከናወን በወሰነው መሰረት ቦርዱ የሰው ሃይል፣ የቁሳቁስ ግዥ፣ የኦፐሬሽን እቅድ፣ የሃብት ምደባን በማከናወን ለዚሁ ምርጫ ሲዘጋጅ ቆይቷል። በዚህም መሰረት ታህሳስ 25 ቀን 2013 ዓ.ም የ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ይፋ የሆነ ሲሆን አጠቃላይ ጊዜ ሰሌዳው ከእቅዱ ለ16 ቀናት ከመገፋቱ ውጪ በታቀደለት ሁኔታ ተከናውኗል ማለት ይቻላል።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ዝግጅት እና ደረጃ ለማሻሻል በርካታ ጥረቶችን ያደረገ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በግልፅ ሚያሳይ ድምጽ መስጫ ሳጥን፣ የድምጽን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ የሚረዳ የድምጽ መስጫ መከለያ፣ የምርጫውን ተአማኒነት ለማሻሻል የሚረዱ በየደረጃው ያሉ የደህንነት መጠበቂያዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ አድርጓል። እነዚህ መቆለፊያ (seals) ፣ መከፈቱ የሚያሳውቅ ቦርሳ እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች የምርጫውን ደረጃ ከፍ ከማድረጋቸውም በላይ ለመጪዎቹ አገራዊ ምርጫዎች የምርጫ ደረጃን ወደኋላ እንዳንመልስ መሰረት የሚሆኑ ናቸው። ለምርጫ ቁሳቁሶች በአጠቃላይ 845 075 945.60 ብር ወጪ ተደርጓል።

**የእጩዎች ምዝገባ እና የፓርቲዎች ተሳትፎ**

የምርጫ፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና ስነምግባር አዋጅ 1162/ 2011 በሚያዘው መሰረት የተከናወነው የፓለቲካ ፓርቲዎች ዳግም ምዝገባ ስራ በሂደት ላይ ከነበሩ አያሌ ፓርቲዎች መካከል የህጉን መስፈርት ያሟሉ ፓርቲዎች፣ ትብብሮች እና ቅንጅቶችን ቁጥር 52 እንዲሆን አድርጎታል። እነዚህ መስፈርቱም ያሟሉ 52 ፓለቲካ ፓርቲዎች በተናጠል እንዲሁም በትብብር/ቅንጅቶቻቸው አማካኝነት 49 የምርጫ ምልክቶችን ወስደዋል። የእጩዎች ምዝገባ ሲጀመርም ከ46 የፓለቲካ ፓርቲዎች በአጠቃላይ 9 ሺህ 505 እጩዎች ተመዝገቡ ሲሆን ከነዚህ እጩዎች መካከል 148ቱ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ሲሆኑ 1 ሺህ 987 ያህሉ ደግሞ ሴት እጩዎች ናቸው። ምዝገባው ቦርዱ በመላው አገሪቷ በከፈታቸው 674 የምርጫ ክልል ቢሮች የተከናውነ ነበር።

የእጩዎች ምዝገባ ሂደት ከተግዳሮቶች የተነጠለ አልነበረም፣ እንደሚታወቀው ምርጫ እና ሂደቱ የብዙ አካላትን ወቅታዊ እና የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳን መሰረት ያደረገ ፈጣን ምላሽ እና ስራ ይጠይቃል። የእጩዎች ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት ከክልል እና ከተማ መንግስታት የሚገኙ ትብብሮች በሰአቱ ባለመድረሳቸው የተነሳ አገራዊው የእጩዎች ምዝገባ ከ የካቲት 08 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ የካቲት 25 2013 ዓ.ም እና ከ ከየካቲት 15 እስከ የካቲት 26 ቀን ድረስ ለሁለት ተከፍሎ ተከናውኗል። በዚህም የተነሳ የእጩዎች ምዝገባ ከተያዘለት ጊዜ ለ 15 ቀናት ያህል የተራዘመ ሲሆን ይህም መጀመሪያም በጠባቡ የታቀደውን የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ ይበልጥ አጣቦታል። የእጩዎች ምዝገባ ሂደትም ወቅት የትራንስፓርት እና ሎጂስቲክስ ችግሮች ምን ያህል ለምርጫው ተግዳሮት ሊሆኑ እንደሚችሉ በትንሹም ቢሆን ለቦርዱ ያሳየ ነበር።

የእጩዎች ምዝገባ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ቦርዱ ለመራጮች እና ምርጫን በአትኩሮት ለሚከታተሉ አካላት መረጃዎችን ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም መሰረት የእጩዎች ምዝገባን የተመለከቱ የሬዲዮን እና ጋዜጣ አምዶችን በማዘጋጀት በ19 ሚዲያዎች አማካኝነት ለ2 ሳምንት ያህል የእጩዎች ምዝገባን እና ምርጫን የተመለከቱ መልእክቶች አስተላልፏል።

የእጩዎች ምዝገባ ወቅት ቦርዱ በአብዛኛው ምርጫን ከሚወዳደሩ ፓርቲዎች 500 በላይ አቤቱታዎችን በመቀበል ያስተናገደ ሲሆን የእጩዎች ምዝገባ ኦፐሬሽን ስራን የሚያግዘው 665 የነጻ የስልክ መስመርን በመክፈትም በቀን እስከ 400 የሚደርሱ ጥሪዎችን እያስተናገደ የምዝገባ ችግሮችን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ።

**የመራጮች ምዝገባ**

የመራጮች ምዝገባን ወደ 50 ሺህ የሚጠጉ ቦታዎች ለማከናወን አቅዶ የተነሳው ቦርዱ ይህንን ስራ ለማከናወን ፍቃደኛ እና ገለልተኛ የሆኑ አስፈጻሚዎችን ለመመልመል ከፍተኛ ተግዳሮት አጋጥሞታል። በዚህ ትግልን በጠየቀ እና ወሳኝ ሂደት ገለልተኛ አስፈጻሚዎችን ማግኘት እና መመልመል የሚቻልበት የሰው ሃይል ስብስብ አለመኖር፣ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የበጎ ፍቃደኝነት ባህል እና እንቅስቃሴ፣ ሂደቱን ለመደገፍ ከፓለቲካ ፓርቲዎች የተገኘው በጣም ውስን ድጋፍ እና ትብብር የምርጫው ሂደት ትልቁ ተግዳሮት ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሆኖም 152 ሺህ 700 ያህል ምርጫ አስፈጻሚዎች ከተወሰኑ ጉድለቶች ጋርም ቢሆን ምርጫውን በትጋት እና በቁርጠኝነት ማስፈጸም ችለዋል። ነገር ግን የአስፈጻሚዎች ምልመላ ላይ ባጋጠመው ከፍተኛ ችግር የተነሳ የመራጮች ምዝገባ መጀመሪያ ቀን ከታቀደለት የካቲት 22 ቀን ወደ መጋቢት 16 ቀን እንዲሸጋገር ሆኗል።

በ42 ሺኀ 585 ያህል ምርጫ ጣቢዎች ላይ የመራጮች ምዝገባ ከተጀመረም በኋላ በምርጫው ካሉ ዋና ዋና ትግበራት መካከል ሲሆን በፈታኝ ሁነቶች የታጀበም ነበር። በዚህም የተነሳ የመራጮች ምዝገባ ሊከናወንባቸው ያልቻሉ የአገራችን ክፍሎች መኖራቸው፣ የመራጮች ምዝገባም ያከናወኑ ክፍሎች የምዝገባው ሂደት ላይ አቤቱታዎች መቅረባቸው፣ የመራጮች ምዝገባ በከፊል ብቻ የተከናወነባቸው ቦታዎች መኖራቸው ከብዙ በጥቂቱ የሚነሱ ናቸው።

የመራጮች ምዝገባ ቁሳቁስ ስርጭት በሚከናወንበት ወቅት የነበረው ከፍተኛ የሎጂስቲክስ እና የትራንስፓርት ተግዳሮች፣ የትብብሮች መዘግየት፣ የመራጮች በምርጫው መጀመሪያ ሳምንታት በዝቅተኛ ደረጃ መመዝገብ እና የመሳሰሉት የመራጮች ምዝገባ ሂደትን ሁለት ጊዜ እንዲራዘም አድርገውት ነበር።

በመራጮች ምዝገባ ወቅት ሶስት በሚዲያ የሚተላለፉ መልእክቶች በ 62 ያህል ሚዲያዎች በዋናነት በ5 ቋንቋ እንዲሁም በትርጉም በተጨማሪ 14 ቋንቋዎች የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻዎች፣ የመራጮች ምዝገባን የሚያበረታቱ 10 አጭር የስልክ መልእክቶች ተላልፈዋል። በዚህም የተነሳ በአጠቃላይ **38,234,910** ያህል መራጮች ሊመዘገቡ ችለዋል።

የእጩዎችም ሆነ የመራጮች ምዝገባን የሚያከናውኑ አስፈጻሚዎች ከቦርዱ ስራቸውን አስመልከቶ ስልጠናዎችን የወሰዱ ሲሆን ለሁለቱም ተግባራት በተዋረድ አራት ደረጃ ያላቸው ስልጠናዎች የተሰጡ ናቸው። እነዚህ ከዚህ በፊት ከነበሩት በልዩ ሁኔታ ሁሉም በምርጫ ሂደት ላይ የሚሳተፉ አስፈጻሚዎች ስልጠናዎች እንዲያገኙ፣ ተግባሩን ራሱን በሚያካናውኑባቸው ቁሳቁሶች ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ ተችሏል። በዚህም የስልጠና ቁሳቁሶች እሽጋ እና ስርጭት ለብቻው የተከናወነ ሲሆን ስልጠናው በየደረጃው በ20 ከተሞች እና በ 674 ምርጫ ክልል ቢሮዎች ደረጃ የተከናወነ ነበር።

**የድምጽ መስጫ ወረቀት አደራደር ሎተሪ እና የድምፅ መስጫ ወረቀት ህትመት**

በ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ከተከናወኑ አዲስ ተግባራት መካከል አንዱ የድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ የሚቀመጠ እጩዎች ተራ የሚያገኙበትን መንገድ በሎተሪ አንዲሆን ማድረግ ነው። ቦርዱ ይኅንን በሎተሪ የእጩዎች ተራ የመወሰን ተግባር ለማካናወን ሲነሳ ሁሉም ፓርቲዎች በእኩልነት እድል የሚያገኙበትን ተምሳሌታዊ አሰራር ለመከተል፣ በተግባሩም ደግሞ መራጮች ምርጫቸውን የሚያገኙበት መንገድ ያለተጽእኖ እንዲሆን ያለመ ነው። በዚህ ሂደት በድምር 1150 ለሆኑ ለክልል እና ለፌዴራል የምርጫ ክልል አይነቶች እጣ የማውጣት ስነስርአት የተከናወነ ሲሆን የድምፅ መስጫ ወረቀቱም በምርጫ ታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የእጩዎችን ፎቶግራፍ እንዲይዝ ተደርጓል። የድምፅ መስጫ ወረቀት ህትመቱ በሁለት አገሮች የተከናወነ ሲሆን በእጩዎች ዝርዝር ማጣራት ወቅት በተፈጠሩ የአሰራር ተግዳሮቶች የተነሳ ካጋጠሙ ችግሮች ውጪ ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ የመራጮች የሚያገኙትን

መረጃ ለመጨመር ጥረት ያደረገ፣ እንዲሁም ፍትሃዊ ውድድርን ለማሳየት ያለመ ሆኖ እንዲሰራ ለማድረግ ተሞክሯል። የድምፅ መስጫ ወረቀት ህትመት 9 ሚልዮን ደላር ያህል ገንዘብ የተመደበ ሲሆን ሙሉ ወጪው የተሸፈነው በአገር ውስጥ በጀት ነው።

**ተሳትፎ**

6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ካሳካቸው ዋና ዋና ቁምነገሮች መካከል ዋናው የብዙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ነው። በሂደቱ ላይ የመራጮች ትምህርት ለመስጠት 169 ያህል ሲቪል ማህበራት እውቅና የወሰዱ ሲሆን 46 ያህል አገር ውስጥ ሲቪል ማህበራት ደግሞ ምርጫውን ለመታዘብ ፍቃድን አግኝተው 44 ሺህ 560 ያህል ታዛቢዎችን በድምፅ መስጫው ቀን አሰማርተዋል።

በፓለቲካ ፓርቲዎች በኩልም ቢሆን ሁሉም ህጎች እና ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከ20 በላይ ውይይቶች የተከናወኑ ሲሆን 16 ያህል ውይይቶች ደግሞ የጊዜ ሰሌዳው ከወጣ አንስቶ በየሳምንቱ ተከናውነዋል። በዚህም ሂደት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፓርቲዎች በርካታ ግብአቶችን እና የውሳኔ ሃሳቦችን ለማግኘት ችሏል።

ቦርዱ በ6ተኛው አገራዊ ምርጫ ዝግጅቱ የመረጃ ፍሰትን እና ግልጸኝነትን ለማሻሻል ያላሰለሰ ጥረትን ሲያደርግ የቆየ ሲሆን የዚህ የመራጮች መረጃ የማግኘት መብት ህጋዊ አካል የሆነውን ስራ ለማገዝም ወደ 70 የሚጠጉ የሚዲያ ተቋማት በ 1 ሺህ 971 ያህል ጋዜጠኞቻቸው አማካኝነት እውቅናን አግኝተው ምርጫውን ሂደት ዘግበዋል። ከነዚህም መካከል 160 ያህል ጋዜጠኞች የአለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ወክለው እውቅና የወሰዱ ናቸው።

በምርጫው ሂደት ላይ በመራጭነትም ሆነ በተመራጭነት ተሳትፏቸው አነስተኛ የሆነ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍም ቦርዱ ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ሲሆን በዚህ ሂደትም ለሴት እጩዎች ስልጠና እና ድጋፍን፣ የአካል ጉዳተኞች አካታችነትን በህግ እና በኦፐሬሽን ማእቀፍ ሲያከናውን ቆይቷል። በዚህ ምርጫ በእጩነት ከተሳተፉ ፓለቲከኞች መካከል 99 ያህሉ አካል ጉዳተኞች ናቸው።

**የድምጽ አሰጣጥ ሂደት**

ከድምፅ መስጫ ቀን አስቀድሞ ከነበሩት የምርጫ ተግባራት ትምህርት በመውሰድ የድምፅ መስጫ ቀን ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳይኖር ቦርዱ ጥረቶችን አድርጓል። በዚህም በኩል የክልል እና የፌዴራል መንግስት አመራሮች ድጋፍ ታክሎበት በሂደቱን በታቀደው መሰረት ማከናወን ተችሏል። በእለቱ በከፍተኛ የመራጮች ተሳትፎ እና በአንዳንድ ቦታዎች በቦርዱ ቅልጥፍና እጥረት የተነሳ መራጮች መንገላታታቸው ቦርዱን በጣም ያሳዘነው እና የአቅም ችግሮቹም ላይ ትምህርት ያገኘበት ሆኖ አልፏል።

በድምጽ መስጫው ቀን 40 ሺህ 365 ያህል ምርጫ ጣቢያዎች የተከፈቱ ሲሆን በነዚህ ጣቢያዎች መራጮች ድምፃቸውን በሰላማዊ መንገድ ሲሰጡ ውለዋል። ቦርዱ በእለቱ ያጋጠሙ ሎጂስቲካዊ ችግሮችን ከስር ከስር በመፍታት መሰረታዊ የሆነ የድምፅ አሰጣጥ ችግር ሳይኖር እንዲጠናቀቅ ማድረግ ችሏል። በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሰኔ 14 ቀን በተከናወነው ድምጽ አሰጣጥ ሂደት መራጮች ምዝገባ ቢያከናውኑም ድምጽ ያልተሰጠባቸው የምርጫ ክልሎች ሲኖሩ በአጠቃላይ በ70 የምርጫ ክልሎች ውስጥ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት አልተከናወነም።

ድምፅ መስጫ ቀን ሂደት ተከትሎ ቦርዱ ከድምጽ አሰጣጥ ሂደት ጋር የተገናኙ ችግሮችን በተለያዩ መንገዶች በመቀበል መፍትሄ ሲሰጥ ውሏል። የድምጽ መስጫ ቀን ካለፈም በኋላ ፍትሃዊ የአቤቱታ መስማት ሂደትን በመከተል አቤቱታዎችን በህግ ባለሞያዎች አማካኝነት ሲቀበል ቆይቷል፣ በዚህ ሂደትም 165 የምርጫ ክልሎች ላይ አቤቱታ የቀረበ ሲሆን አቤቱታውን በማደራጀት ለፓለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ያደረገ ሲሆን የቀረቡለትንም ማስረጃዎች አይቷል። ከ30 ፓርቲዎች እና 7 የግል እጩዎች የቀረቡት አቤቱታዎች በዋናነት አስተዳደራዊ እርምጃን፣ የውጤት ስረዛን እና ድጋሚ ምርጫን የጠየቁ ናቸው።

ቦርዱ በአጠቃላይ ሂደቱ ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ የአሰራር ግድፈቶችን መርምሮ እርምጃዎች የወሰደ ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው

- 10 ምርጫ ክልሎች ላይ የድጋሚ ቆጠራ እንዲከናወን አዟል እነዚህም መካከል 3ቱ የተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ክልሎች ናቸው። እነዚህም

    1. ደንቢያ 1 - አማራ ክልል ተወካዮች ምክር ቤት
    2. ባኮ ጋዘር 1 - ደ/ብ/ብ/ህ/ክ ተወካዮች ምክር ቤት
    3. ድሬደዋ 2 - ድሬደዋ ከተማ ተወካዮች ምክር ቤት
    4. አፋምቦ፣ አሚባራ፣ አብአላ፣ ኮነባ፣ ጉሊና - አፋር ክልል የክልል ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች
    5. ጆር ምርጫ ክልል - የክልል ምክር ቤት ጋምቤላ
    6. ሸርቆሌ ምርጫ ክልል- የክልል ምክር ቤት ቤኒሻንጉል
    7. ቁጫ ምርጫ ክልል - የክልል እና የተወካዮች ምክር ቤት ቆጠራ ላይ ያለ [1]

-11 ያህል ምርጫ ክልሎች ላይ የታየው የአሰራር ግድፈት ውጤት ሊቀይር እንደሚችል በመገንዘብ የድጋሚ ምርጫን ለማከናወን ወስኗል። እነዚህ ውሳኔዎች የተሰጡባቸው የምርጫ ክልሎችም የታዛቢዎች እና ወኪሎች መከልከል፣ ምርጫ ሂደቱ በአካባቢው መስተዳድር መዋቅር ተጽእኖ ስር በመውደቁ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መራጭ እንዳይመርጥ ክልከላ መደረጉን ቦርዱ በምርመራው በማመኑ የተወሰኑ ናቸው።

እነዚህም

አማራ ክልል የተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች -

- መርጦ ለማርያም
- አዴት
- ራያ ቆቦ
- ባቲ
- ሞላሌ
- እስቴ 3 [2]

[1] ይህ ሪፓርት በቀረበበት ወቅት ቁጨ ምርጫ ክልል በማእከል ቆጠራ ላይ ነው።

[2] ይህ ምርጫ ክልል ሪፓርቱ በቀረበበት ሰአት ሳይነበብ የተዘለለ ነገር ግን በቦርዱ ለድጋሚ ምርጫ የተወሰነበት ነው

አፋር ክልል

- ዳሉል የክልል ምክር ቤት

ቤኒሻንጉል

- መንጊ ምርጫ ክልል- የክልል ምክር ቤት

ደ/ብ/ብ/ህ/ክ

- ምስቃንና ማረቆ 2 (ተወካዮች እና ክልል ምክር ቤት)
- ቡሌ (ተወካዮች እና ክልል ምክር ቤት)
- ባስኬቶ ልዩ (ተወካዮች እና ክልል ምክር ቤት)

**ተግዳሮቶች እና ስኬቶች**

6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ለማከናወን ከዝግጅቶቹ ጀምሮ በሂደቱ ላይ በርካታ ተግዳሮቶች አሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከዚህም መካከል

- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተረከበው ዝቅተኛ የማስፈፀም አቅም ካለው ተቋም አንፃር የተቋም ግንባታን እና የምርጫ ዝግጅትን በጋራ በአጭር ጊዜ ለማካሄድ መስራት
- በመላው አገሪቷ ለሚከናወን ትልቅ ሁነት የቦርዱ የሰራተኞች እና የልምድ አቅም ውስነንት
- የምርጫ ሂደቱ ወቅት የፓለቲካ ሂደቱን ውድድር ሚዛን የሚያስቱ የተለያዩ ተግባራት (በዝቅተኛው የመንግስት መዋቅር የሚገኙ የመንግስት አካላት በሂደቱ ላይ ጣልቃ ለመግባት መሞከር፣ (የህዝብ እና የግል ሚዲያዎች ላይ በጉልህ የታዩ ወገንተኛ ዘገባዎች…ወዘተ)
- በአገራችን የሚገኙ የፀጥታ ችግሮች የተነሳ በተወሰኑ የምርጫ ክልሎች ላይ ድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከሌሎች ምርጫ ክልሎች ጋር በተመሳሳይ ቀን አለመከናወኑ
- በተለይ ከድምፅ አሰጣጥ ሂደት ጋር በተገናኘ በዝቅተኛ እርከን ደረጃ የፓርቲ ወኪሎችን ስራቸውን የማደናቀፍ ተግባር መታየቱ
- መሰረታዊ የምርጫ ደረጃዎችን (Basic electoral standards) ባለመረዳትም ሆነ በመረዳት በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ የአቅም ችግር መኖሩ
- ምርጫው በሚካሄድበት ወቅት እጅግ በጣም ብዙ፣ ፓለቲካዊ፣ ወታደራዊ እና ማህበራዊ ሁነቶች አብረው በመከናወናቸው የምርጫውን ሂደት በብዙ ሁነቶች ማሃል በብቃት ለማስፈፀም የመቻል አቅምን መጠየቁ

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ቢኖሩም ምርጫውን ሰላማዊ እና ተአማኒ ለማድረግ ከፍተኛ ልፋትን ጠይቋል ፣ በዚህም ቦርዱ ራሱ የሚኮራባቸው ዋና ዋና ስኬቶች መመዝገባቸውንም አብሮ ማስታወስም ያስፈልጋል፣

ከነዚህም መካከል

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቦርዱ ከዚህ በፊት ከነበረው ፍፁም በተለየ ከወገንተኛ ፓለቲካ ገለልተኛ የሆነ ተቋም ለመመስረት ያደረገው ጥረት የተሳካ እና የሚያኮራ መሆኑ
- ቦርዱ ምርጫን ዘመናዊ ለማድረግ ወደኋላ ለመመለስ የማይቻሉ አዳዲስ አሰራሮችን ማስተዋወቁ ለወደፊቱ ምርጫዎች እጅ የሚጠቅም መሆኑ
- በምርጫ ሂደት ያልተቋረጠ ውይይትን በማድረግ ከፓለቲካ ተዋናያን በተለይም ደግሞ በፓለቲካ ፓርቲዎች እምነትን ለማትረፍ ቦርዱ ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉ
- በፀጥታ ችግሮች፣ የፓለቲካ ጠርዘኝነት ከፍተኛ በሆነበት በዚህ ወቅት ሰላማዊ እና ተአማኒ ምርጫን ማስፈፀም መቻሉ ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

**የ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ውጤት**

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተቋቋመበት አዋጅ 1133/ 2011 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀፅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1162 አንቀጽ 62 መሰረት የሚከተለውን ውጤት ይፋ አድርጓል።

(የውጤት ሰንጠረዥ ከዚህ ሪፓርት ጋር ተያይዟል)

**ምስጋና**

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉትን የሚከተሉትን አካላት ለማመስገን ይፈልጋል።

1. በ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ በከፍተኛ ቁጥር ድምፃቸውን ለሰጡ ዜጎች
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰራተኞች
3. 6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ላይ የተሳተፉ የምርጫ ክልል አስተባባሪዎች፣ የዞን አስተባባሪዎች፣ ምርጫ አስፈጻሚዎች
4. በ6ተኛው አጠቃላይ ምርጫ ለተሳተፉ ፓርቲዎች እና እጩዎች
5. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ተወካዮች ምክር ቤት
6. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት
7. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የምርጫ ፀጥታ ታስክ ፎርስ
8. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር
9. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ሃይል
10. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
11. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትራንስፓርት ሚኒስቴር
12. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራል ፓሊስ
13. ሁሉም የክልል መንግስታት እና የክልል የጸጥታ አካላት
14. የምርጫውን ሂደት የታዘቡ እና የመራጮች ትምህርትን ያከናወኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች
15. የኢትዮጵያ አየር መንገድ
16. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
17. ኢትዮ- ቴሌኮም
18. የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን
19. የኢትዮጵያ ፓስታ አገልግሎት ድርጅት
20. 6ተኛው አጠቃላይ ምርጫን የዘገቡ የህዝብ እና የግል ሚዲያዎች እና ጋዜጠኞች
21. ሙቨ ዋን ሎጂስቲክስ
22. አካካስ ሎጆስቲክስ
23. አንድነት በቦሌ የኤርፓርት ካርጎ ጉምሩክ ሁለገብ አገልግሎት
24. ሰለሞን ዘውዴ መርከብ እና እቃ አስተላላፊ ወኪል
25. ሰጎን ማእሪል ኢንርናሽናል ሙቨርስ
26. የኔነህ ሙላት የህግ ቢሮ
27. ቤዛ ሽዋንግዛው የህግ ቢሮ
28. ያለለት ተሾመ የህግ ቢሮ
29. ሎሚ ፕሮዳክሽን
30. ዘሌማን ፕሮዳክሽን

31. ሪዞልዩሽን ስቱዲዮ
32. ዲቴል ዲዛይንስ
33. የኮንስትራክሽ ባለሞያዎች ማህበር
34. የአርክቴክት ባለሞያዎች ማህበር
35. የኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል
36. የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና የፕሮግራሙ ሲድስ ፕሮጄክት (SEEDs project)
37. የአሜሪካን መንግስት ተራድኦ (USAID) እና አለም አቀፍ የምርጫ ስርአት ፋውንዴሽን (IFES)
38. የአውሮፓ ህብረት (EU) እና የአውሮፓውያን የምርጫ ድጋፍ ማእከል (ECES)
39. የጀርመን መንግስት የኢትዮጵያ ሚሽን
40. ኒሚድ - Netherlands institution for multi-party democracy
41. ኦፕን ሶሳይቲ ፋውንዴሽን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ሐምሌ 03 ቀን 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ